" ቡቃያው "
( Germinal )

ደራሲ - ኤምሊ ዞላ
ተርጓሚ - ሙሉብርሃን ታሪኩ

ሐምሌ 26/11/2012

በጋዜጣዉ ሪፓርተር እደተዘገበው።

ሰሞኑን የኀትመት ብርሃን ካዩት መጻሕፍት አንዱ ‹‹ቡቃያው›› የሚል ርዕስ የተሰጠው የኤሚሊ ዞላ ልቦለድ አንዱ ነው ፡፡

በእናት ቋንቋው ጀርሚናል (Germinal) የተሰኘውን መጽሐፍ የተረጎሙት ሙሉ ብርሃን ታሪኩ ናቸው ፡፡ ተርጓሚው ስለመጽሐፉ በሰጡት ሐተታ ኤሚሊ ዞላ ‹‹ቡቃያ›› የሚል አንድምታ ያለውን ቃል “Germinal” ለርዕስ የመረጠው ላብ አደሮችን ከዘመናት የጭቆና ቀንበር የሚያላቅቅ አዲስ የሰው ዘር መብቀሉን ለመጠቆም በማሰብ ነው፡፡

‹‹ጀርሚናል›› የሚለው ቃል በፈረንሳይ አብዮት የነውጥ ዘመን በሁሉም ዘንድ በጉጉት የሚጠበቀውን ኅብረተሰባዊ ህዳሴ ለማመላከት የተመረጠ ነበር ፡፡

በአዲሱ የፈረንሳይ አብዮት የዘመን ቀመር " ጀርሚናል " ሰባተኛ ወር ሲሆን የፀደይ ወቅት መግቢያን በመጠቆም ከመጋቢት አጋማሽ እስከ ሚያዝያ አጋማሽ ይዘልቃል፡፡

ኤምሊ ዞላ በተለይ ለመጠቆም የፈለገው ወቅት በድህረ አብዮቱ ዘመን በሚያዝያ 1795 ሲሆን የፓሪስ ላብ አደሮች አመፅ ያሰሙበትን ቀናት የሚያስታውስ በርዕሱም ማኅበራዊ እኩልነትን የሚያረጋግጥ አዲስ ማኅበረሰብ እንደሚበቅል ለመተንበይ የሞከረበት ነው ፡፡

በተርጓሚው ማብራሪያ እንደተጠቀሰው፣ በሥነ ጽሑፍ " ተፈጥሮአዊ ፍልስፍናኡኤ " (Naturalism) ዘውግን በዘመኑ ያበለፀገው ዞላ መሆኑ ይታወቃል ፡፡

በዚሁ ፍልስፍና የሰውን ልጅ ባህርያት ለመተንተን ተፈጥሮ ሳይንስን መሠረት ያደረገው ዞላ እንደ ትላቁ ፈላስፋ ባልዛክ ሁሉ እርሱም የሰውን ልጅ ከመኖሪያ አካባቢው መስተጋብርና አካላዊ እንቅስቃሴ አንፃር ለመግለጽ ተጠቅሞበታል፡፡

ኤሚሊ ዞላ በሞንሱ የነበሩ የከሰል ማዕድን ሠራተኞችን አኗኗር በሥዕላዊ መንገድ የገለጸበት ሥራው እንደሆነ፣ በዚሁ መጽሐፍ የሞንሱን ነዋሪዎች ጉስቁልና በተፈጥሮአዊ ገሃድ ፍልስፍናው ማሳየቱን፣ የዞላ ገፀ ባህርያት የሆኑት ማዕድን ቆፋሪዎች ለረዥም ዓመታት በኖሩበት የሥራ ጫናና የጉስቁልና ሕይወት ባህርያት አመለካከታቸው ቅርፅ መያዙን አሊያም ቅርፅ አልባ መሆኑ በጥልቀት ተገልጿል፡፡

ደራሲው በዚህ መጽሐፍ ከዳሰሳቸው በርካታ ሁነቶችና ክስተቶች መካከል በይበልጥ የሚጠቀሱት ተፈጥሮአዊ ፍልስፍና፣ በዘር (መወለድ) የሚወረስ ባህርይ፣ የኢንዱስትሪ ቀውስ፣ የሶሻሊዝምና አናርኪዝም ተፅዕኖ እንዲሁም በዘመኑ የነበረው የሁለተኛው የፈረንሳይ ኢምፓየር አስተዳደራዊ ችግሮች ይገኙበታል፡፡

በመጽሐፉ አፅመ ታሪክ እንደጠቀሰው መጽሐፉ በሠራተኞች አመፅና በማኅበረሰቡ ጊዜያዊ መውደቅ ላይ ያተኩራል ፡፡ በከበርቴና ላብ አደር መደቦች መካከል የሚደረገውን ትግል ተጠቅሞ የሃያኛውን ክፍለ ዘመን አንገብጋቢ ጥያቄ አስቀድሞ የሚተነብይ ነው ::

ቡቃያው የአንድ ዘውግ ጽሑፍ ብቻ አይደለም በአንድ ጥላ ሥር በርካታ የጥናት ዘርፎችን የያዘ እንጂ፡፡

መጽሐፉ የሁሉንም ዘመን አንባቢ የሚመጥን ሥራ ለመሆን የበቃው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ታሪካዊ ርዑሳነ ጉዳያትን በአንድ ላይ በመያዙ ነው ፡፡ በዚህ ልቦለድ ሥራው ኤሚሊ ዞላ አንባብያንን በምናብ አጓጉዞ የማይታወቅ የከሰል ቆፋሪዎች ዓለም ውስጥ በመውሰድ፣ አንባቢው የገፀ ባህርያቱን የሕይወት ድራማ አብረው እንዲኖሩት ማድረግ ችሏል ።

